AABE
Accounting and Auditing Board of Ethiopia
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ

ከኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

ኢኮኖሚ

# የሒሳብ ሙያ ነጻነት እና ቀጠናዊ ትስስር

ቀደም ባለው እትማችን የአገልግሎት ግብይት ነፃነት ለአኅጉራዊ ውህደት ያለውን አስተዋጽኦ ለመመልከት ሞክረናል፡፡ የሒሳብ ሙያ አገልግሎት (ሊበራላይዜሽን) ነጻነት በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ገጽታ ላይ እየተጠናከረ የመጣ ጽንሰ-ሀሳብ፣ በሒሳብ አያያዝ ኢንዱስትሪ ውስጥ ተወዳዳሪነት እና ፈጠራን ለማበረታታት ገበያዎችን መክፈትን እና ቁጥጥሮችን ማላላትን የሚያበረታታ ሥርዓት ነው። በብቃት እና በራስ መተማመን ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን፣ የተጠቃሚ አካላት የአገልግሎት ፍላጎት ማርካትን ያማከለ እንዲሁም የተጋነነ የዋጋ ንረትን በማመጣጠን የተረጋጋ ሙያዊ ዲሲፕሊን እንዲኖር ማድረግ ተጠቃሽ ፋይዳዎቹ እንደሆኑ ይጠቀሳል፡፡

በዛሬው እትማችን የሂሳብ ሙያ ነጻነት ከአገልግሎት ግብይት ነጻነቶች/Accountancy Service Liberalization/ አንዱ እንደመሆኑ መጠን የዘርፉ ነጻነት ለኢኮኖሚው እና ለውጤታማ ቀጠናዊ እና አኅጉራዊ ትስስር ያለውን ፋይዳ እንደሚከተለው እናያለን፡፡

የሒሳብ ሙያ አገልግሎት ነፃ መውጣት በዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓት ውስጥ ከሚጠቀሱ የአገልግሎት ዘርፎች ነፃ መውጣት እንደ ዋነኛ ምሰሶ የሚጠቀስ ዘርፍ ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡ ይህም የዓለም ንግድ ድርጅት ካስቀመጣቸው አጠቃላይ የንግድ ስምምነቶች ውስጥ አጠቃላይ የአገልግሎት ግብይት ስምምነት (General Agreement of Trade in Services) አንዱ ሲሆን የሙያዊ አገልግሎቶች አካል የሆነው የአካውንተንሲ ሙያ አገልግሎት ነፃነት (Accountancy service liberalization) ደግሞ ሌላው የሙያ ዘርፍ ነው፡፡

### የሒሳብ ሙያ አገልግሎት ነፃነት ማለት ምን ማለት ነው?

በቀላል አገላለጽ አገልግሎቶች (የመጓጓዣ/ትራንስፖርት፣ የቱሪዝም፣ የኮሙኒኬሽን፣ የባንኮች/ፋይናንስ፣...አገልግሎቶች) እንደማንኛውም የሸቀጥ ንግድ ለግብይት የሚቀርቡ ዘርፎች መሆኑን መተማመን ከተቻለ ሙያዊ አገልግሎቶችም (የሕክምና፣ የማማከር፣ የአካውንታንሲ፣ የምሕንድስና፣ የሕግ፣...አገልግሎቶች) ለግብይት የሚቀርቡ አእምሮአዊ የንግድ ዘርፎች መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡ ይህን ዘርፍ ነፃ ማድረግ ማለት ገደቦችን በማንሳት ያለምንም ከልካይ ድንበር ተሻግረው እንዲሠሩ የመጫወቻ ሜዳውን ለባለሙያዎቹ እና ለኩባንያዎች መክፈት ማለት ነው። የአካውንተንሲ ሙያ ኢንዱስትሪውን የገደቡትን የተለምዶም ሆነ የዘመኑ የሚመስሉ፣ ወቅቱን እና በተለይ ኢኮኖሚውን የማይመጥኑ “መሰናክሎች እንደማፍረስ” ማለት ነው።

ይህ እንግዲህ በማደግ ላይ ላሉት ሀገራት ጫናው የተወሳሰበ ነው፡፡ የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ የባለሙያው መሪ ተዋናይነት እና የግሉን ሴክተር ሙሉ ተሳታፊነትን የሚጠይቅ በበሳል የድርድር ጥበብ እና ክህሎት የሚታጀብ፣ በሩ አንዴ ከተከፈተ መልሶ መዝጋቱ የሚያስከትለውን ውጤት ቀድሞ በማለም የሚከናወን እንደሆነ ይነገራል፡፡ ስለዚህ በውህደት ውስጥ የምናገኛቸው ጥቅሞች ብቻ ሳይሆኑ አደጋዎችም እንዳሉ ቀድመን ከተረዳን በራችንን ዘግተን የምንኖርባት ዓለም ግን አሁን ላይ ያለች አይመስልም፡፡

> **ክልከላዎች (Protectionism) በሀገር ውስጥ ያሉ ለጋ (Infant) ኢንዱስትሪዎችን እንዳያዳክሙ ብሎም ከገበያ እንዳያስወጡ፣ የስራ እድልን እንዳያጠፉ እና የባለሙያ “ካለ“ ፍልሰትን (Brain Drain) እንዳያባብሱ አስፈላጊ ቢሆኑም እና በተመረጡ አቅም ባልዳበረባቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሆኑ ባያጠያይቅም ግን ደግሞ በጊዜ ካልተገደቡ እና ተወዳዳሪነትን የማያበረታቱ ከሆነ የሚያስከትሉት አደጋ ከፍተኛ ነው**

### የአገልግሎት አቅርቦት ዓይነት በዓለም ዓቀፉ የንግድ ድርጅት (WTO) ዕይታ

(ሀ) ከአንድ የንግድ ድርጅቱ አባል ሀገር ወደ ማንኛውም ሌላ አባል ሀገር የሚደረግ የአገልግሎት አቅርቦት፤ Mode 1, Cross Boarder Service Supply, በቴሌኮሙኒኬሽን እና በዘርፉ ቴክኖሎጂ የሚከናወን ድንበር ዘለል የአገልግሎት አሰጣጥ ዓይነት ነው፡፡ ማንኛውም የመረጃ አገልግሎት ፈላጊ በኤሌክትሮኒክስ እና በዘመኑ የተግባቦት ቴክኖሎጂ ከተለመደው አገልግሎት ውጪ በድርጅቱ አባል ሀገራት መካከል በሚደረግ ስምምነት ማግኘት የሚቻል የአገልግሎት አቅርቦት ዓይነት ነው፡፡

(ለ) በአንድ የድርጅቱ አባል ሀገር ውስጥ ለማንኛውም አባል ሀገር አገልግሎት ሸማች/ፈላጊ የሚሰጥ የአገልግሎት ዓይነት ነው፡፡ Mode 2, Consumption Abroad, እንደ ቱሪስት፣ የሕክምና፣ የትምህርት... አገልግሎት ለማግኘት የመሳሰሉ፣

(ሐ) በአንድ አባል ሀገር አገልግሎት ለማቅረብ ቅርንጫፍ ቢሮ መክፈት፣ በትብብር መስራት... Mode 3, Commercial Presence. ለምሳሌ በጁባ ከተማ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ከፍቶ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት፡፡

(መ) የሰዎች በአካል በስፍራው በመገኘት አገልግሎት መስጠት Mode 4, Physical presence in person ናቸው፡፡ ከአራቱ የአገልግሎት አቅርቦት ዘዴዎች የሒሳብ ሙያ አገልግሎት በየትኛው ዓይነት የሚፈፀም መሆኑን አውቆ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ በአራተኛው ዓይነት ከተባለ ምን ዓይነት ስምምነት ነው የሚፈፀመው፣ አገልግሎቱን በአካል ተገኝቶ ለማቅረብ ወደ የትኛው ሀገር ምን ዓይነት የመግቢያ ፈቃድ፣ ለምን ያክል ጊዜ፣ ለምን ዓይነት ተቋም (ለተወሰነ ተቋም ብቻ ወይስ ለሌሎችም አገልግሎት መስጠት ይቻላል ወይስ...) የሚሉትን መለየት ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ነው በባለፈው እትማችን የአገልግሎት ነፃነት ማለት ልክ እንደ ሸቀጥ ነፃነት በገቢ ምርቶች/ሸቀጦች በተወሰነ መቶኛ ቀረጥ እንደመቀነስ ቀላል አይደለም ያልነው፡፡ ስምምነቱ በአንድ ጊዜ ብቻ የሚሳካ ሳይሆን ከላይ በተጠቀሱት ላይ ተደጋጋሚ የሆነ የድርድር ጥበብንም የሚጠይቅ ነው፡፡

ዛሬ በፍጥነት በማደግ ላይ ባለው የዓለም ኢኮኖሚ፣ የአካውንተንሲ ዘርፉ የፋይናንስ ግልፅነትና ጤናማነትን፣ ተገዢነትን እና በንግድ ግብይቶች ላይ ታማኝነትን በማረጋገጥ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ዘርፉ ትክክለኛ የፋይናንስ መዝገቦችን በተገቢው በመያዝ፣ ለውሳኔ ሰጪ አካላት በተጨባጭ እውቀት ላይ የተመሰረተ ፋይናንስ እና ፋይናንስ ነክ መረጃዎችን ለማቅረብ እና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ጉልህ ሚና አለው።

ነገር ግን የተለመዱ የቁጥጥር ማዕቀፎች እና የክልከላ ፖሊሲዎች ብዙውን ጊዜ በሙያ አገልግሎቶች እድገት እና ፈጠራ ላይ ለውጥ ሲያሳዩ አይታይም። ዘርፉ ብዙውን ጊዜ ለፈጠራ እና ውድድር እንቅፋት ያጋጥመዋል ምክንያቱም ጥብቅ የቁጥጥር ስርዓቶች፣ የፍቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች ከሀገር ሀገር የተለያዩ መሆን እና የገበያ ተደራሽነት እጥረት፣ ውሱን የሙያ ዝግጅቶች እና የመሳሰሉ መሰናክሎች አዳዲስ ተዋናዮች ወደ ገበያው/ሙያው እንዳይቀላቀሉ እንቅፋት ሊሆኑ እና የአዳዲስ የአገልግሎት አቅርቦቶችን እድገት ሊገድቡ ይችላሉ።

ክልከላዎች (Protectionism) በሀገር ውስጥ ያሉ ለጋ (Infant) ኢንዱስትሪዎችን እንዳያዳክሙ ብሎም ከገበያ እንዳያስወጡ፣ የስራ እድልን እንዳያጠፉ እና የባለሙያ ”ካለ” ፍልሰትን (Brain Drain) እንዳያባብሱ አስፈላጊ ቢሆኑም እና በተመረጡ አቅም ባልዳበረባቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሆኑ ባያጠያይቅም ግን ደግሞ በጊዜ ካልተገደቡ እና ተወዳዳሪነትን የማያበረታቱ ከሆነ የሚያስከትሉት አደጋ ከፍተኛ ነው፡፡ አቅም አልዳበረም በሚል ሰበብ የሚፈፀም ክልከላ ለጥገኝነት እና ለጠባቂነትን የሚገፋፉ፣ ከዓለም ዓቀፍ የንግድ ሥርዓቱ ተወዳዳሪነት ከማግለሉም ባለፈ በዓለም ዓቀፍ የንግድ ሥርዓቱ ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ የማሳጣቱ አጋጣሚም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ የአቅም ውስንነት ዓለም ዓቀፍ ሥርዓቱን በማጥናት ቅድመ-ዝግጅት ማድረግን የሚጠይቅ እና በልበ-ሙሉነት ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ይፈልጋል፡፡

የሒሳብ ሙያ ዘርፉን ነፃ ማውጣት የተዋንያኑን የመለወጥ ፍላጎት በመገንዘብ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት እና ለዘርፉ ባለሙያዎችም ሆነ ለሪፖርት አቅራቢ አካላት በተመጣጣኝ ዋጋ የተሻለ የአገልግሎት ጥራት ለማግኘት አማራጭ እድሎችን ለማስፋት የቀረበ ነው። ይህ በአኅጉራዊ እና ቀጣናዊ ትስስር ዕይታ ሲታይ የቀጣናው አባል ሀገራት ሙያዊ አገልግሎቱን ለማቅረብ የእርስበርስ ስምምነት በመፍጠር የሚፈፅሙት ስርዓት ማለት ነው፡፡ ቀጣናዊም ይሁን አህጉራዊ ውህደትን ወይም ትስስርን እናፋጥን ከተባለ ለዚህ መሰረት የሆኑ ሙያዊ እና የሌሎችም አገልግሎቶች ግብይቶች፣ የሸቀጦች እና አእምሮአዊ ንብረቶች ነፃነትን ማጠናከር ከብዙ አንዱ ነው፡፡

ጤናማ እና በጥናት ላይ የተመሰረተ፣ በየትኛው ቀጣና ምን ዓይነት ምርት ወይም አገልግሎት በብዛት እና በጥራት፣ ምን ዓይነት ፍላጎት እና አቅምስ በሚያስፈልገው መልኩ ይገኛል የሚል የራስንና የሌላውን ወገን አቅም አስቀድሞ በመለየትና በዚያው ልክ መስራት ለስምምነቱ ውጤታማነት አጋዥ ይሆናል፡፡ ለዚህ ነው የአፍሪካ ሕብረት የምንፈልጋት አፍሪካን በ2063 አንድ እናደርጋታለን ብለው “AFRICA UNITE” ፕሮጀክት ቀርፀው እየሰሩ ያሉት፡፡

ውህደቱን ለማሳለጥ በተለምዶም ይሁን በዘመነ አሰራር ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉትን መሰናክሎች በሂደት በ”ድርድር” በማስወገድ የንግድ (የሸቀጥ/የአገልግሎት) እንቅስቃሴያችንን የጋራ መጠቃቀም መርህን Mutual benefit በመከተል እና ሙያዊ ስነ-ምግባር በመላበስ የድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

ዘርፉን ነፃ ማድረግ ማለት ግን በዘፈቀደ የሚገባበት በነፃ የተገኘ ዕድል አድርጎ ማሰብ ደግሞ የጥፋቶች ሁሉ ጥፋትን ለማስተናገድ እንደመዘጋጀት ነው፡፡ የበርካታ ጥቅሞቹ ተቋዳሽ መሆን የሚቻለው ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶቹን መቋቋም ሲቻል ነው፡፡ የዓለም ንግድ ድርጅት ነፃነትን ማወጅ ብቻ ሳይሆን በነፃነት ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ ነፃነቱ የሚያስከትሉትን አላስፈላጊ ግጭቶችን የሚያስወግድበት ፕሮቶኮልም አለው፡፡

### ሉላዊነት /ግሎባላይዜሽን/ በሒሳብ ሙያ አገልግሎቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ግሎባላይዜሽን ወይም ሉላዊነት በሂሳብ አያያዝ ዓለም ውስጥ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ኃይል ነው። የንግድ ድርጅቶች ተደራሽነታቸውን በማስፋፋት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲሰሩ እንከን የለሽ እና ደረጃውን የጠበቀ የሒሳብ አገልግሎት ፍላጎት ከመቼውም ጊዜ በላይ ልዩ ቦታ የሚሰጡት የሙያ ዘርፍ ነው። እነዚህ ዓለም አቀፍ ፍላጎቶች በብቃት እና በጥራት መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሒሳብ አገልግሎትን ነፃ ማድረግ ቁልፍ ሚና ነው።

ባለሀብቶች ሀብታቸውን በተሻለ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በማስገባት ዕድገታቸውን በአትራፊነት ለማስቀጠል እና ከራሳቸውም አልፎ ሀገራት ከፍተኛ የሆነ የስራ አድል ለዜጎች በመፍጠር ድህነትን ለመዋጋት እና ሰላማዊ ኑሮ ለማስቀጠል በሚጥሩበት ዘመን ድርሻቸውን ለመወጣት የቢዝነስ እንቅስቃሴያቸው የተሻለ አቅም እና ልምድ ባላቸው ተወዳዳሪ በሆኑ ባለሙያዎች እንዲመሩላቸው ይፈልጋሉ፡፡

ዓለም አንድ መንደር በሆነችበት እና የቴክኖሎጂ ምጥቀቱ ሰዎችን ከገበያ ለማስወጣት በሚያደርገው ከፍተኛ ትንቅንቅ ውስጥ ባለሙያዎች የሙያውን ስነምግባር በማክበር እና በየጊዜው ከሚሻሻሉ እና አዳዲስ ከሚወጡ የዘርፉ ዓለም ዓቀፍ ስታንዳርዶች ጋር እራሳቸውን በማብቃት በራሳቸው የሚተማመኑ ተወዳዳሪ ባለሙያዎችን ማግኘት የቅድሚያ ቅድሚያ ነው፡፡

የተለያዩ ተቆጣጣሪ አካላትም የሒሳብ ሙያ አገልግሎቱን ነፃ በማድረግ ሂደት ውስጥ የቁጥጥር ማዕቀፎቹን ግልፅ እና የሚያሰራ መሆኑን ማረጋገጥ እና የሚተገበሩ ደረጃዎችን ማስከበር ወሳኝ ነው። ቁልፍ ተቆጣጣሪ አካላት እና ደረጃዎችን የሚያዘጋጁ ድርጅቶች የኢንዱስትሪውን ገጽታ በመገንባት ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። በተለያዩ ገበያዎች ውስጥ ወጥነት እና ጥራትን ለማረጋገጥ ቁጥጥር እና ደረጃዎችን ማጣጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የአካውንተንሲ አገልግሎቶች ነፃነት/liberalization በመሠረቱ በሒሳብ ሙያው ኢንዱስትሪ ውስጥ የቁጥጥር ማዕቀፎችን የማላላት እና ገደቦችን በሂደት በመቀነስ ገበያውን ነጻ ማድረግ ማለት ነው፡፡ የሒሳብ ባለሙያዎች ክንፋቸውን ዘርግተው በነጻነት ወደ ሌሎች ግዛቶች ተዘዋውረው እንዲሰሩ በመልቀቅ አገልግሎታቸውን ከድንበር አልፈው እንዲሰጡ ማድረግ ማለት ነው። የዚህ ትልቁ ተግዳሮት ሊሆን የሚችለው ያለምንም ቅድመ-ዝግጅት በውሱን አቅም ተወዳዳሪ ባልሆነ እና ባልሰለጠነ የአሰራር ዘይቤ ገበያውን ክፍት የማድረግ ውሳኔ ላይ መድረስ ነው፡፡

የሒሳብ ሙያ አገልግሎት ነፃነት ለሒሳብ ድርጅቶች እና ባለሙያዎች አዳዲስ አማራጮችን ይፈጥራል። ኩባንያዎች ተደራሽነታቸውን እና የአገልግሎት አድማሳቸውን እንዲያሰፉ የሚያስችላቸው ወደገበያው የመቀላቀያ በር እና የማስፋፊያ እድሎችን ማብዛት ነው። ግለሰቦች የበለጠ ነፃ በሆነ አካባቢ ተወዳዳሪ ሆነው ለመቆየት ሲጥሩ ሙያዊ እድገት እና ክህሎትን ማሻሻል ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ። ያለንባትን ዓለም እውነታ አይናችንን ገልጠን በማየት እና የወደፊቱን እየተነበይን ቀድመን መዘጋጀት ይጠበቅብናል፡፡ ኢትዮጲያ ትልቅ ሀገር ነበረች ብቻ ሳይሆን አሁንም ትልቅ ናት፡፡ የእኛ (የዘርፉ ባለሙያዎች እና ተዋናዮች) ድርሻ ግን ሚናው ትልቅ ነው፡፡